REGION KRONOBERG

**ያደባ የሳንባ ነቀርሳ፥ ለበሽተኛ የሚሰጥ መረጃ (2016-09-19)**
**የቅድሚያ መከላከል ህክምና በሚሰጥበት ወቅት።**
*የተላላፊ በሽታ ሓኪሞች፥ የተላላፊ በሽታ መከላከያ ልሳን።*

**ኣንድ ሰው በሽታው እንዴት ይተላለፍበታል?**
የሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ የሚዛመተው በዓየር ውስጥ ነው። ይህ የሚሆነው በበሽታው የተለከፉውና ማጋባት የሚችል ሰው ሲስልና፥ በቅርቡ የሚገኝ ሰው ባክቴሪያውን በትንፋሹ ሲስብ ነው።

**ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?**
ነቀርሳው የተላለፈባቸው ሰዎች ሁሉ አይታመሙም። የብዙ ሰዎች ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከያ ኃይል ባክቴሪያው እንዳያድግና እንዳይሰራጭ ሊገታው ይችላል። በዚህ መልኩ ባክቲሬያው ሰውነት ውስጥ እያለ ኣድብቶ ይቀመጣል። በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ነው ያደባ ሳንባ ነቀርሳ የሚባለው።

**ያደባ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ኣይደለም**
ከደም ምርመራ (IGRA-Test) ወይም ከቆዳ ምርመራ (Tuberkulintest)  በኋላ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ኣለብዎት ከተባሉ **ሙሉ በሙሉ** ጤነኛ ነዎት ማለት ይቻላል። እናም በሽታውን ወደ ሌላ ሰው ማጋባት ኣይችሉም። ይሁን እንጂ በሕይወት እስካሉ ድረስ በሽታው ኣንድ ቀን ሊከሰት ይችላል የሚል ስጋት ይኖራል፥ ሆኖም ይህ የሚያጋጥምበት ዕድል በጣም የመነመነ ስለሆነ ኣብዛኛዎቹ ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች ህክምና ኣይደረግላቸውም።

**በኣንዳንድ ሁኔታ የቅድመ መከላከል ህክምና ሊሰጥ ይችላል**
ኣንዳንድ ሰዎች ላይ በሽታው ኋላ ሊከሰትባቸው ይችላል የሚል ስጋት በእጅጉ ካለ የቅድመ መከላከል ህክምና እንዲያደርጉ ይጋበዛሉ። ይህ ህክምና የሚደረግው በቅድሚያ ለህፃናትና ለታዳጊዎች ሲሆን ከእርግዝናና ከወሊድ ጋር በተያያዘ ምክንያትም ይሰጣል። በተጨማሪም የተፈጥሮ በሽታ የመከላከል ኃይላቸው የተዳከመባቸው ለምሳሌ፥ የካንሰር ህክምና የሚያደርጉ፥ ኢንሱሊን የሚወስዱ የስኳር በሽተኞች፥ ከባድ የኩላሊት ችግር ያለባቸው ሰዎችም ይደረግላቸዋል። የቅድመ መካላከል ህክምና ኣንዳንድ ጊዜ በቅርብ ጊዜ የሳንባ ነቀርሳ ለያዛቸው ሰዎችም ይደረጋል።

**የቅድመ መከላከል ህክምና እዲያደርጉ ይመከራሉ**
ያደባ ሳንባ ነቀርሳ ስላለቦትና ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች ውስጥ ስለሚገኙ በሽታው እንዳይከሰት ማድረግ ላይ ባለመ የቅድመ መከላከል ህክምና እንዲያደርጉ ይመከራሉ። ይህን እንዲያደርጉ የሚመከሩት ወደ ፊት በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ለመጠቃት ያለዎን መጥፎ ዕድል ስለሚቀንስ ነው።


***smittskyddsenheten***
Centrallasarettet, 351 85 Växjö. ☎0470-588278